## ግልጽ ደብዳቤ ለኣምባሳደር ብርሃኑ ከበደ ፡ ሎንዶን።

ከምስማኩ ተሊላ፤ ሎንዶን። ሰኔ 18 ቅን 2001 ዓ ም።

ክቡር አንባሳደር፡

## ጉዳዩ፡ በ እንግሊዝ ፓርላማ በ ኢት ዮጵያ ሁኔታ ስለተደረገው ውይይት፤

የኢትዮጵያ ኤንባሲ ለንደን መኖሩን አውቃለሁ፡ ግን የወቅቱ አንባሳደር እርስዎ መሆንዎን ያወቅሁት እረቡ ሰኔ 10 ቀን ለአሜሪካን ራዲዎ በሰጡት ቃለምልልስ ነው። ቃለምልልሱን የሰጡበት ጉዳይ ማክሰኞ ስኔ 9 ቀን 2001 በእንግሊዝ ፓርላማ ውስጥ “የሶስተኛ አለም ትብብር” (THIRD WORLD SOLIDARITY) የሚባለው ሕዝባዊ ስብስብ “ሰባዊ መብት በኢትዮጵያ” በሚል አጠቃላይ አርእስት በአካሄደው ውይይት ላይ ነበር። ይህን ስብሰባ በቅርብ ስለተከታተልኩትና፡ የእርስዎንም ቃለምልልስ በጥሞና ስላዳመጥኩት “ሆድና ጀርባ” የሆኑ ጉዳዮችን ስለአስተዋልኩና ዝም ብሎ ማለፍም የተሳከረ ኢንፎርሜሽንን እንደ “እውነት” መቀበል ሆኖ ስለታዬኝ የበኩሌን ግንዛቤ በቅድሚያ ለለንደኑ ብትን ኢትዮጵያዊ (LONDON DIASPORA) ምንአልባት ስፋ ባለ መልኩ ደግሞ ቃለምልልሱን ለአቀረበው የአሜሪካ ድምጽ ራዲዎ አድማጮች ለማካፈል ነው። እንደርስዎ ላለ ከፍተኛ ባለስልጣን ደብዳቤ ስጽፍ ይህ የመጀመሪያ ጊዜዬ ባይሆንም ግልጽ ደብዳቤ ኣድርጌ ማቅረቤ በግልጽ ያቀረቡትን ቃለ ምልልስ ለሰሙ ሁሉ ጉዳዩን ለማካፈል እንጅ ከአንድ ዬዲፕሎማሲ ሞያተኛ ጋር አታካራ ለመፍጠር እንዳሌሆነ እርስዎና አንባቢዎች እንዲረዱልኝ እጠይቃለሁ።

## ስብሰባው በማን ለምን የት ተዘጋጀ?

እንደርስዎ አባባል ስብሰባው የተካሄደው ሳብራ መሓመድ ለምትባል የዛሬ 18/17 አመት ከኢትዮጵያ ለቃ እንድትወጣ (persona non-grata) ለተደረገች ሴት ዕርዳታ እንዲደረግላት ጠይቃ የተዘጋጀ ነው ብለዋል። በተጨማሪም “የሶስተኛ አለም ትብብር” (THIRD WORLD SOLIDARITY) የተባለው ስብስብ አመታዊ የራት ግብዣ በማዘጃጀት ላይ ስለሆነ እሱን ለማስተዋወቅ ነው ብለዋል። ስብሰባው የተካሄደው በክፍል ቁጥር 14 ነው፡ ብለውም በእርግጠኛነት ተናግረዋል።

ከብር መጋፋት አይሁንብኝ እንጅ ይህ ያሉት ሁሉ ስህተት ወይንም ውሸት ነው። በቦታው የተገኙት የሚታወቁትና የማይታወቁት ስላዮች የነገሩዎት ይህን ከሆን አሳስተዎታል። ስብሰባውን ለማቃለል ሆን ብለው እርስዎ ያደረጉት ክሆነ ደግሞ ያለቦታዎ ወርደው ተራ የፕሮፓጋንዳ ስራ እየሰሩ ነው። እንደ እርስዎ ያለ ከፍተኛ ዲፕሎማት እንዲህ አይነቱን ስህተት በእርግ|ጠኛነት በራዲዎ ከመናገሩ በፊት የፕሬስ ሃላፊው ጉዳዩን ከነመረጃው አጣርቶ እንዲአምጣ ማዘዝ ትክክለኛ አካሄድ ነበር። እራሴው አደርገዋለሁ ብለው ከተነሱ ደግሞ ጉዳዩን በቅጡ ማጥናት ያስፈልጋል። የሚአገለግሉት መንግስት (ግንባር ማለት ትክክል ሳይሆን አይቀርም) ከሚወቀስባቸው ብዙ ነገሮች አንዱ በመስረተቢስ ፕሮፓጋንዳ ሕዝቡን ማደንቆሩ ነው።፡ይህ የእርስዎ አቀራረብ ደግሞ ይህን ክስ አጉልቶና አጠናክሮ በተደረጉት ንግግሮችና ለቀረቡት ትችቶችና ክሶች ማጠናከሪያ ሆነ እንጂ መመለሻ አልሆነም።

በመጀመሪያ “ለሶስተኛው አለም ትብብር የሁሉ ፓርቲዎች የፓርላማ ቡድን (All-Party Parliamentary Group on Third World Solidarity) አላማው ከታዳጊ አገሮች ሕዝቦች ጋር ትብብርን ለማዳበር፡ በዲፕሎማቲክ ሥራ ስላምን ለማጠናከር፡ በተጨማሪም ስብአዊ መብትን ሠላምንና ትክክለኛ ፍርድ እንዲስፋፉ ለማድረግ እንደሆነ መቓቓሚያ ደንቡ ይዘረዝራል፡፡ የወቅቱ ሊቀመንበር ዴቭድ አንደርስን ናቸው።

“የሶስተኛ አለም ትብብር” (THIRD WORLD SOLIDARITY) የሚባለው ሕዝባዊ ስብስብ ደግሞ በፖለቲካ አንቀሳቃሾቺና በምሁሮች የተቋቋመ፡ አላማዉም ለስላም፡ ለመቻቻል፡ ግጭቶችን በውይይትና በዲፕሎማሲ ለመፍታት ጥረት የሚአደርግ የሲቢክ ማህበር ነው። በአሁኑ ጊዜ ሊቀ መንበሩ ካውንስለር ሙሽታክ ላሻሪ ናቸው።

እነኝህ ሁለት ድርጅቶች አጠቃላይ አላማቸው ተመሳሳይ የሆነ በአደረጃጀታቸው ግን አንዱ ከሌላው ነፃ ሆነው የተቋቋሙ ናቸው። ከዚህ በመነሳት የመደጋገፍ አካሄድ አላቸው። በተለይ “የፓርላማው ስብስብ”፡ “የሶስተኛ አለም ትብብር” ስብስብን በልዩ ልዩ መንገድ ይረዳል። ከዚህ አንዱ በእንግሊዝ ፓርላም ህንጻ የስብስባ ክፍል እንዲአገኙ መርዳት ነው።

እንግዲህ በእንግሊዝ ፓርላም ህንጻ ኢትዮጵያን አስመልክቶ የተደረገውን ስብስባ ያዘጋጀው “የሶስተኛ አለም ትብብር” (THIRD WORLD SOLIDARITY) ሲሆን፡ የፓርላማው ቡድን ደግሞ ባለው የትብብር አካሄድ የመስብስቢያ ቦታውን ይዞአል። እንደ እስፖንስር ደግሞ “ለሶስተኛው አለም ትብብር የሁሉ ፓርቲዎች የፓርላማ ቡድን” ሊቀ መንበር ዴቪድ አንደርስን ስብስባውን በሊቀ መንበርነት ከፍተዋል።

“የሶስተኛ አለም ትብብር” (THIRD WORLD SOLIDARITY) የሚባለው ሕዝባዊ ስብስብ” አባል ሆነው የሚስሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞችና በትውልድ ኢትዮጵያውያን በዜግነት ግን እንግሊዝ የሆኑ ስዎች አሉ። ከነዚህ አንዱዋ ለረጂም ጊዜ አባል ሆነው የቆዩት ወ/ሮ ሳብራ መሓምድ ናቸው። ኢትዮጵያን በሚመለክት ዉይይት እንዲደረግ ለረጂም ጊዜ ሲሞክሩ የኖሩ ኢትዮጵያዊያን ናቸው። በመጨረሻም ስምምነት ተደርሶ ኢትዮጵያውያን ስደተኞችና ያካተተ ኮሚቲ ተቋቊሞ የማክስኞ ስኔ 9 ቀን ስብስባ እንዲጠራ አድርጎአል። የስብስባው ዋና አላማ በ3 ዋና ጉዳዮች ላይ ጥናቶች/ንግግሮች ቀርበው ውይይት እንዲካሄድ ነው። በስምምነት የተመረጡት አርእስቶች ፲ኛ/ ጀኖሳይድ፡ 2ኛ/ የስብአዊ መብት መጣስ በኢትዮጵያና፡ 3ኛ/ ምርጫና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ፤ ሲሆኑ፡ የቀረቡትም ንግግሮች ከሞላ ጎደል ይህን ያጠቃለለ ነበር።

የስብስባው አጠራር በድሕረ ገጾች በኢሜልና በራዲዎ ስለሆነ ለማንም ክፍት የሆነ፡ ልዩ መጥሪያና የመግቢያ ወረቀት የማያስፈልገው ነጻ ስብስባ ነበር። ከኤንባሲ የመጡት ስዎች ሲገቡ ማንም የጠዬቃቸው የለም። ተስብሳቢው ወደ ፓርላማው ሲገባ ፎቶግራፍ እየተነሳ ምስሉን በአንገቱ እንዲአንጠለጥል ከመደረጉ በስተቀር መታወቂያ እንኳን አይጠዬቅም ነበር። ለስብስባው መጀመሪያ የተያዘው ክፍል ቁጥር 14 ሲሆን በቀኑ ግን የስው ቁጥር ከተገመተው በላይ ስለሆነ (ሁለት መቶ ያህል ስው ነበር) ወደ ትልቁ መስብስቢይ አዳራሽ (The Grand Meeting Room) ተዛውሮአል።

በንግግርዎት እየደጋገሙ ጥሪ አልተደረገልንም እያሉ ያቀረቡት ስሞታ መስረተ ቢስ ነው። እንዲያው ኢትዮጵያን በሚመለክት በሚደረጉ ስብሰባዎች ሁሉ ለኤንባሲ የተለዪ ጥሪ መደረግ አለበት ብለው ያስባሉ መስል። ምንአልባት በርስዎ እይታ ሁሉም ስብስባ እንደ ብሪቲሽ-ኢትዮጵያ የሁሉም ፓርቲዎች ስብስብ እየመስለዎት ክሆነ አሁንም ስህተት ነው። የዚአም ሁኔታ ጠሪና ተጠሪ የራሱ አካሄድ አለው። የብሪቲሽ-ኢትዮጵያ የሁሉም ፓርቲዎች ስብስብ በአላማ ያስቀመጣቸው 2 ነገሮች ሲሆኑ አንዱ በእንግሊዝና በኢትዮጵያ ያሉትን የፓርላማ ተመራጮች ማገናኘት፡ ሁለተኛ ደግሞ በሁለቱ ሕዝቦች መካክል መቀራረብ እንዲኖር መጣር ነው። እስካሁን የሚታዬው የፓርላማ ተመራጮች መገናኘት እንጂ የሕዝቦች አይደለም። በዚህም ግንኙነት ሕዝብና የሕዝብ ወገን የሆኑ ሁሉ እኛም ካልተገኘን አይሉም፡ ግንኙነቱ የተመራጮች ነውና። እንግዲህ የአዲስ አበባን ፓርላማ ስዎችን ተመራጭ ብለን ክወስድናቸው ነው። እኛም ውጭ ያለነው ጠጂ እና ዶሮ ወጥ ከአዲስ አበባ ትጭኖ መጥቶ በእንግሊዝ ፓርላም ግቭዣው ሲትረፈረፍ ጋብዙን አንልም ልካችን እናውቃለንና። እኛ ስድተኞች ነን። ልኩን የማያውቅ እርስዎ የሚወክሉት መንግስት ነው። ላስረዳ። በአንድ በኩል ተራብን ምግብ እርዱን እየተባለ በሌላ በኩል ደግሞ አገራቸው ድረስ ምግብና መጠጥ ተሸክማችሁ መጥታችሁ በእንግሊዝ ፓርላማ ብሉልን ጠጡልን ትላላችሁ። ይህም የሚሆነው በስልጣን ላይ ያለው ግንባር ስብስቦ በፓርላማ መልክ ያስቀመጣቸውን ስዎች ክብረ ሞገስ ለማላበስና እንደ ፓርላማ ተቀባይነት እንዳለው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማሳዬት እንጅ እውነት የአቻ ግንኙነት ሆኖ አይደለም። የእንግሊዝ መንግስት እኮ በመንግስታት አመዳደብ፤ ያለውን የኢትዮጵያ መንግስት ሲደለድል “ተስባሪ መንግስት” (Fragile State) በሚል ክፍል ነው ያስቀመጠው። ስለሆነም መጠራት መጋቨዝ ወዘት ትርጉም ሊኖረው የሚችለው አቻ ለአቻ ሲሆን ነው። ስለሆነም ስደተኛው ኢትዮጵያዊ ኤንባሲን አልጋበዘም ብለው እንደ ስህተት ብቻ ሳይሆን እንደ ጥፋት ከቆጠሩት መስረታዊ ችግር አለ ማለት ነው። ላስታውስዎትና በቅርቡ ለንደን ኤንባሲ በረከት ስሞኦንን ሊስሙ የመጡትን ጥቂት ስደተኞች አትገቡም ብላችሁ በፖሊስ አስከለከላችሁአቸው። እንደ ሌላው ሁሉ ነገር መጋበዝ አለመጋበዝን እንደፈለጋችሁ መጠቀም ትፈልጋላችሁ። አይቻልም። በቃ። የእናንተ አካሄድ ዲያስፖራውን ብቻ ሳይሆን ህዝብን በአብዛኛው አንገፍግፎታል። በቃኝ ብሎአል።

ይህ ሁሉ ሲባል ደግሞ ኤንባሲው እርስዎ እንደሚሉት አልተጠራሁም ብሎ ተስብስቦ አልተቀመጠም። ዝቅተኛ ጀሌዎቹን ልኮ ወሬ ሲአስለቅም እንድነበር በስብስባው ላይ ዬተገለጠ ሁኔታ ነበር። ስዎቹ ተነስታችሁ ተናገሩ ቢባሉ በጅ አላሉም። ከሁሎም ወገን አይደለሁም የሚል አንድ ስደተኛ ተነስቶ አዳራሹን በእርምጃ እያማተረ እርስዎ እንደተናገሩት ስብሰባው ሚዛን የጎደለው ነው ሲል በትቢት ተወጥሮ ተናግሮአል። ሌላ ነጥብ ስላልነበረው ይህንኑ የሚዛን ጉዳይ እየደጋገመ በመናገሩ አጠገቡ የነበሩ ወጣት ሴቶች በቃህ ቁጪ በል ሲሉት ተደምጠዋል። አንዱዋ ወጣት የስውዬው አነጋገርና ሁኔታ ስለአናደዳት ስቅስቅ ብላ ስታለቅስ በአካባቢው የነበሩት ስዎች በስውዬው አባባል ተቃውሞአቸውን ገልጸዋል። ክቡር አምባሳደር ይህን ሁኔታ ነው ስውዬውን ሊደበድቡት ተነሱ

፤ ቆዬት ብለው ደግሞ ደበደቡት፤ ብለው የተናገሩት ውሸት ነው። ያስገምታል። እንድዚህ ኣይነት የውሸት ክስ ከአንድ ከፍተኛ ዲፕሎማት የሚጠበቅ አይደለም። ያሳዝናል።

ኢይጋ ፎረም የሚባለው የወያኔ የውጭ ፕሮፓጋንዳ ክፍል ደግሞ ይህንኑ ስብሰባ አስመልክቶ ፊአስኮ በሚል አርእስት በአዎጣው አጭር የፕሮፓጋንዳ ጽሁፍ የሚጠላቸውን ሰዎች ለመስደብ ተጠቀመበት እንጂ የጻፈው አንድም እውነት የለበትም። ተናገረ የሚለው ሰውና የለጠፈው ፎቶግራፍ የተጭበረበረ ነው። ሌላም የጨመረው ሁሉ ውሸት ነው። ይህ አይነት "የበሬ ወለደ" ወሬ በጠባብ የወያኔ ተባባሪዎች ሲነገር ይህ የመጀመሪያ አይደለም። ይህ ሕሊናና ሞራል የሌለው ስብስብ ቢመከሩትም ስለማይሰማ መሞከሩ አጉል ድካም ነው። ወደፊት ግን መከራ ይመክረዋል።

ክቡር አምባሳደር፤ ስደተኛው ኢትዮጵያዊ ሆነ በአገር ያለው የሙብቱ መጣስ ጉዳይ ቅጥያጣ እጅግ ከመጠን ያለፈ ለመሆኑ ነጋሪ አያስፈልገውም። የግፉ ሰለባ ያልሆኑ ሰዎችና የግፍ አድራጊው ተባባሪዎች በተጎዳው ወገን ላይ ከሚአፌዙበት ይልቅ በመፍትሄ ፍለጋው አስተዋጽዎ ቢአደርጉ ይሻላል። ሲክር ይበጠሳል ነውና የጊዜውን የበላይነት እንደ ዘላለማዊ አድርጎ መመልከት ብዙ ችግር እንድሚአስከትል ከወዲሁ ማወቅ መልካም ነው። በስተቀር ኢትዮጵያን ዛሬ "ተስባሪ መንግስት" (Fragile State) የሚል ስም እንድታገኝ ያደረጋችሁ ወገኖች ነገ ይህ ሁኔታ እውን ከሆነ የህዝብ መተላለቅ ሃላፊነቱ ሙሉ በሙሉ በእናንተ ላይ እንደሚወድቅ ማስብ ያስፈልጋል።

ስደተኛው ሎቢ አድርጎ በሰብአዊ ሙብትና በመጪው ምርጫ ዙሪያ ውይይት አደረገ ሲባል እኛ ካልተጠራን የሚለው የይገባኛል ጥያቄ ያለቦታውና ያለአግባብ የቀረበ ነው። የወያኔን መንግስትና ተወካዩችንማ ነገ በአለም አቀፍ የፍትህ ፍርድ ቤት (ICC) ላይ ነው ሕዝብ መከራከር የሚፈልገው። የለንደኑ ስብስባ ለዚአኛው መንደርደሪያ እንዲሆን የተደረገ ጥረት እንጂ ስለ ሰባዊ ሙብት መጣስ በለንደን ክርክር ለመክፈት አይደለም።

## በስብሰባው ማን ተገኘ፤

ሌላው ነገር ደጋግመው የተናገሩት ደግሞ የእንግሊዝ ፓርላማ ሰዎች፤ ቢቢሲ፤ ሲኤንኤን፤ አልነበሩም፤ አልተገኙም፤ ያሉት ነው። እንዴት አውቁ? ያስብሰባ እኮ ከፍተኛ የመንግስት መግለጫ የሚሰጥበት ሳይሆን ስደተኛ ኢትዮጵውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ተሰብስበው ስለ ሰው እሊቂት፤ ስለ ሙብት መረገጥ፤ ስለመጭው ምርጫና አካዬዱ ውይይት ለማድረግ የተዘጋጀ ነው። የሚዲያ ባለሙያዎች በእንዲህ አይነት ስብስባ መታዎቂአቸውን በአንገታቸው አጥልቀው፤ ካሜራ ተሸክመው፤ አብሪ አስከትለው አይመጡም። የሚመጡት ውይይቱን ለመከታተልና ወደፊት ለሚአደርጉት ስራ የሚጠቅማቸውን ኢንፎርሜሽን ለመስብሰብ ነው። ስብሰባው ላይ በስማቸው የተጠሩ እንግዶች ነበሩ። እንዲሁ ተቀምጠው ያዳምጡ የነበሩ ሌሎች ብዙዎች ነበሩ። ከነበረው የውጭ ሰው ስንቱ ጋዜጠኛ፤ ስንቱ የፖለቲካ ሰው እንደሆነ ማወቅ አይቻልም ነበር። እርስዎ ግን ስብሰባውን ለማጣጣልና አልተሳካም ለማለት ጋዜጠኞችና፤ የፓርላማ ሰዎች፤ ዲፕሎማቶች፤ አልተገኙም ብለዋል። የምናውቃቸውን የኢትዮጵይ ኤንባሲ ሰዎች አልተገኙም ብለዋል። ይህ ግምት ውስጥ ያስገባል።

ክቡር አንባሳደር፤ ምርጫው እዬተቃረበ ሲሄድ ውይይቱና ክርክሩ፤ በውስጥም በውጭም ቢስፋፋ ለዴሞክራሲ እድገት ይረዳል። አማራጭ የለለው፤ ተወዳዳሪ ያልተናገረበት፤ የመንግስት ፖሊሲ የማይተችበት ምርጫ እንደ ዴሞክራሲ ምርጫ ሊታይ አይችልም። አሁን እየታዬ ያለው አካሄድ የ97 ሁኔታ እንዳይደገም መከላከል ነው። ይህ እኛ የለለንበት፤ እኛ ያላዘጋጀነው ስብሰባ እያላችሁ የምታነሱት ነገር የ97ቱ ሁኔታ እንዳይደገም የምታድርጉ እርምጃ ነው። ሕዝብ በተለይ ደግሞ ዳያስፖራው ኢትዮጵዊ ይህን የዎያኔ/ኢሕአዴግ አካሄድ አበክሮ እንዲታገለው ያስፈልጋል።

ምርጫና ዬምርጫን ውድድር በተመለከተ ህዝብ የሚጠብቀው ከ97 የተሻለ ሂደት እንዲሆን እንጂ ከዚያ ያነስ እንዲሆን አይደለም። ይህ ከሆነ ሕዝብን ከያዘው የዴሞክራሲ መንገድ ይልቅ ወደ አምጽ እንዲዞር መግፋት ነው። ይ ህ ደግሞ ጫካውን እናውቀዋለን ለሚለው ወገንም አስቸጋሪ ሳይሆን አይቀርም። መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ ተብሎ የሚፌዝበት ጊዜ አልፎአል። በመጨረሻም እርስዎ ምርጫንና ዴሞክራሲን አስመልክቶ እስተናገሩ ድረስ የኔም ትችት ከዛሬው ፈጠንና ጠንክር ባለ እንደሚቀጥል ይገንዘቡልኝ።

EthioLion.Com